# እግዚአብሔር ይመስገን

ከቀመሩ ደሳለኝ

እግዚአብሔር ይመስገን ይላል ክርስቲያን
አልሃምዲኒላሂ የሚለው ሙስሊማን
የእውነት አምላክን ማመስገን ፈጣሪን
ክብር ለሱ ይሁን ክብሩ ይስፋልን
ኢትዮጵያን አየልን መንፈስ ቀረበን።

እናመስግነው እግዚአብሔርን በደስታ በዕልልታ
ጎበኘልን ኢትዮጵያን፣ አየልን በይቅርታ
እንቀበለው በምስጋና ነጭ ለብሰን ቀስተ ዳመናውን ደርበን
እናመስግን ሁላችን ለፈቃዱ ፣ ለቸርነቱ ክብር ምስጋና ለጎበኘን

የኢትዮጵያ አምላክ አዬ የተዘረጉ እጆችዋን
የልቧን ፍቅር ጥንካሬ የእምነቷን
ሰማ ለመናዋን የተማጸነችውን
ፈቃዱ ሆነ አወረደ ምህረቱን፡

እግዚአብሔርን እናመስግን በደስታ በዕልልታ
ዳር እስከዳር በኢትዮጵያ ለሚያሳየን ይቅርታ
እናመስግን ነጭ ለብሰን ቀስተ ዳመናውን ደርበን
ስለጎበኘን ፈጥኖደራሽ በምህረቱ
ስለአዬልን ኢትዮጵያን በአምላክ ዓይኑ መለኮቱ

እናመስግን እግዚአብሔርን በደስታ በዕልልታ
ነጭ ለብሰን ቀስተ ዳመናውን ደርበን በደስታ
ለቸርነቱ ደራሽነት፣ ለጥበቃው የዘወትር ስጦታ
እናመስግን አምላክን በደስታ በዕልልታ።

እናመስግን አምላክን ፣ስለስማ ገዳማቱን
ስልጎበኘ ኢትዮጵያን ፣ስለ ባረከ መሬቲቱን
ስለስማ የሕዝብ ፀሎቱን፣ ስለ አዳመጠ ጩሀቱን
እናመስግን ሁላችን ነጭ ለብሰን አምሮብን
እናመስግን አምላክን በቸርነቱ ለአዬን
እግዚአብሔር ይመስገን ክብር ለሱ ይሀን
ይመስግን ፈጣሪ ክብሩ ይስፋልን።

እናመስግነው አምላክን ስለጎበኘ ኢትዮጵያን
እናመስግን ፈጣሪን ነጭ ለብሰን አምሮብን
እግዚአብሔር ይመስገን ክብር ለሱ ይሁን።